# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም

**መግለጫ**

**የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ሁለተኛ የፐሌነም ስብሰባውን አካሄደ!!**
**በተሳካ ሁኔታም ተጠናቀቀ**

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ከጥር 20 – 21 ቀን 2003 ዓ.ም. የሁለት ቀን የፐሌነም ስብሰባውን አካሂዶ በተሳካ ሁኔታ አጠናቀቀ።

ይህ የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባላት ሁለተኛ ፐሌነም፣ በኢትዮጵያ ሀገራችን የሕዝቧ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ተከብሮ፤ በነዚህም መብቶቹ አማካይነት ሕዝቡ የሥልጣን ምንጭ የሚሆንበት ሥርዓት ዕውን ይሆን ዘንድ ሲታገሉ የወደቁትን (በሀገራችን በከተማና በገጠር፣ በውጭ በጎረቤት አካባቢና እንዲሁም በተለያዩ አህጉራት የነበሩ የኢሕአፓ/ኢሕአሰ/ኢሕአወሊ) አባላትና ደጋፊዎቹን እንዲሁም ሀገር ወዳድ የሆኑ ዜጎቻችንን ለማስታወስ የአንድ ደቂቃ የሕሊና ፀሎት በማድረግ ነበር የተከፈተው።

የፐሌነሙ ስብሰባ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ፤ የአካባቢ፣ የአህጉራዊና የአለም አቀፍ ሁኔታዎችን በተመለከተ በስፋት የዳሰሰ ውይይትን አካሂዷል። ያሳደሩትን ተፅዕኖና ያስከተሉትንም ጉዳቶች በሰፊው ገምግሟል። ከትግላችን አኳያም እየተነተነ ሰፊ ግንዛቤን ጨብጧል፡፡ በተለይ በቅርቡ በቱኒዝያ የተቀሰቀሰው የለውጥ እሳት ከራሱ አልፎ የቅርብ ጎረቤት በሆኑት በአልጄሪያና በግብጽ አልፎም እስከ ጆርዳንና የመን ድረስ የሚገኙ በሥልጣን ላይ የተቆናጠጡ ገዥዎችን እየለበለበ መሆኑን በጥልቀት በመዳሰስ በርካታ ግንዛቤዎችን በመጨበጥ በሀገራችን ሊያስከትል የሚችለውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ክስተቶችን ተመልክቷል። ከወዲሁ አስፈላጊና ተገቢ የሆኑ የተግባር ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ የሚገባ መሆኑንም በማስመር አስፈላጊውን መመሪያና እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል።

ፐሌነሙ ከሀገር ቤቱ ጀምሮ በጎረቤት አካባቢ፣ በአውሮፓ፣ በሰሜን አሜሪካና በኦሺያኒያ ካሉ ተቋማቱና የተግባር ኮሚቴዎች የቀረቡለትን ዘገባዎች በጥሞና አዳምጦ በጥልቀት መርምሯል። በአሁኑ ወቅት ትግሉን በከፍተኛ ደረጃ ለማስቀጠል በፅናት የሚንቀሳቀሰው ኢሕአፓ፣ ካለፈው በተሻለ ሁኔታ ላይ በመገኘቱ መዋቅሩንም ለማስፋፋት ከሚያደርጋቸው ጭብጥ እንቅስቃሴዎቹ በደከመበት መንስኤዎቹን ነቅሶ በማውጣት፤ ጠንከር ብሎ በተገኘበት ደግሞ የሚጎለብትበትን ሁሉ በመለየት ጥልቅ ግንዛቤ ላይ ደርሷል። ይህም ተግባራዊ እንዲሆን አስፈላጊ ባላቸው የሥራ መመሪያዎችም ላይ ወስኗል። በመዋቅርና በአሰራር ጥያቄዎች ዙሪያ ሰፊ ውይይት ያካሄደው ይህ ፐሌነም የፓርቲውን የፖለቲካና የድርጅት ሥራን፣ የሕዝብ ግንኙነትን፣ የፋይናንስና የኤኮኖሚ ጥያቄን፣ የውጭ ግንኙነትን፣ በፍኖተ ዴምክራሲ የሬዲዮ ስርጭቱ የሚደረጉ የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ተግባራትን አስመልክቶም አስፈላጊ ላላቸው ለውጦችና ማሻሻያዎች፣ የተግባር መመሪያዎችን ወስኗል። ለመመሪያዎቹ ተግባራዊነትም ጥብቅ ክትትል እንዲደረግባቸው አጽንዖት ሰጥቶበታል።

የስብሰባውን ሰፊ ጊዜና ትኩረት በመውሰድ ፐሌነሙ የተወያየበት ሌላው ዋና ነጥብ፣ በዘረኛው ጠባብ አምባገነን ቡድን የሚመራው የወያኔ አገዛዝ ላለፉት 20 አመታት በሚያካሂድበት አረመኔያዊ ጭፍጨፋ፤ በመልካም አስተዳደር እጦትና በዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እየደረሱበት ያሉት የተለያዩ አሰቃቂ በደሎች፤ በየጊዜው እያሻቀበ በሚሄደው የዋጋ ግሽበት ጭምር ሕዝባችን በኑሮው እየተጎዳ ገቢው በየጊዜው እያሽቆለቆለና ለመቋቋም እያቃተው መሆኑን ነው። በርካታ ወጣቶች በተለይም ሴቶች ይህን ኑሯቸውን ለማሻሻል ከሚልና የአምባገነኑን አገዛዝ በመሸሽ ከውድ ሀገራቸው ለመሰደድ በሚያደርጉት ሙከራና በስደትም ላይ ለተለያዩ በደሎችና ለሞት ጭምር እየተዳረጉ መሆናቸውን በሀዘን አጢኗል። መፍትሄዎች ምን መሆን እንደሚገባቸውም በመጠቆም ለስኬታማነታቸው የጀመረውን ቆራጥ ትግል በፅናት መቀጠል መሆኑንም አስምሮበታል። የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ሁለተኛ ፐሌነም ስብሰባ የተቃዋሚ ኃይሎች በአሁኑ ወቅት የሚገኙበትን ሁኔታና የኃይል አሰላለፍ በሚገባ በመገምገም አጢኗል።

በመጨረሻም የወያኔ አስከፊ አገዛዝ በባዕዳን በመደገፍ ዴሞክራሲያዊ ገፅታ ለመስጠት እየተካሄደ ያለው ጥረት ባለፉት 20 አመታት እንዳልሰራ ፍንትው ብሎ እየታየ ያለበት ሁኔታ ላይ እንደምንገኝ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቸውም ጊዜ በላይ ግልጽ ሁኗል። በመሆኑም ይህን አስከፊ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ አሽቀንጥሮ ለመጣል፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ መሆንና በኢትዮጵያዊነቱ - ጠላቶቹም ሳይቀር አሌ የማይሉት - የማያወላውል አቋም ያለው ለዚህም ሰፊ ሕዝባዊ ድጋፍን የተጎናጸፈው ድርጅት ኢሕአፓ፣ በፐሌነሙ ያገኘውን አዲስ የመንፈስ ፅናት አንግቦ ትግሉን በቆራጥነት የሚቀጥል መሆኑን እንደገና በማስረገጥ የፐሌነሙ ፍፃሜ ሆኗል።

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ትግል ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኖራለች!!

እናቸንፋለን!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France